የሰ.መ/ቁ. 62332

ቀን 29/9/ 2003 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች** ፡- አቶ ዘለቀ ካሣዬ - አልቀረቡም

**ተጠሪ** ፡- የፌዴራል ዐ/ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክስ ሲሆን በፌ/ከ/ፍ/ቤት ቀርቦ የነበረው በቸልተኝነት ሰው በመግደል የሚል ነበር፡፡ ዐቃቤ ሕጉ አቅርቦት የነበረው ክስ ተከሳሽ /የአሁን አመልካቹ / የትራንስፖርት ማሻሻያ ደንብ ቁ . 279/56 አንቀጽ 35 እና የ1996 ዓ/ም ወ/መ/ህግ አንቀጽ 543 /3/ የተመለከተውን ተላለፎ የሚያሽከረክረው ታርጋ ቁ 1-10432 አ/አ የሆነውን መኪና ታህሳስ 20/01 ዓ/ም ከጥዋቱ አንድ ሰዓት ተኩል ላይ በዮሐንስ ቤተክርስቲያን ልዩ ስሙ ሰባራ ባቡር እየተባለ በሚጠራው አካባቢ በእግረኛ ማቋርጫ ዜብራ ላይ ቅድሚያ ባለመስጠት ተክሉ ጌታሁን የተባለውን በቸልተኝነት ገጭቶ ገድሎአል የሚል ነበር ፡፡

ክሱን የሰማው የፌ/ከ/ፍ/ቤት ተከሳሽ የቀረበበትን ክስ ድርጊቱን መፈፀሙን አምኖ ግን ጥፋቱ ያለመሆኑን ስለካደ የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቶ በወ/መ/ሕግ አንቀፅ 59/1/ /ሀ/ እና 543/3/ ስር ጥፍተኛ ነው በማለት የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ተቀብሎ በአንድ አመት ከ6 ወር ፅኑ እስራትና ብር 10,000 / አስር ሺህ/ እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የፌ/ዐቃቤ ሕግ ቅር በመሰኘት ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅረቦ ፍ/ቤቱም ካከራከረ በኃላ ቅጣቱ በአምስት አመት ፅኑ እስራት ከፉ አድርጐ የወሰነ እና የገንዘብ መቀጮውን ባለበት ያልተነሳ መሆኑን ወሰኗል ፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካች በጠበቃው አማካኝነት ህዳር 14 ቀን 2003 ዓ/ም 3 ገፅ ማመልከቻ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ የተለያዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን በማቅረባችን የከፍተኛው ፍ/ቤት ከግምት አስገበቶ ቅጣት የቀለለና ከመነሻው ዝቅ ብሎ መቅጣቱ ግልፅ ሆኖም እያለ ጠቅላይ ፍ/ቤት ተጐጅን ወደ ሕክምና ቦታ መውሰድ በሕግ ማለትም በወ/መ//ሕግ ቁ . 575/2/ ሥር የተጣለበትን ኃላፊነት መወጣቱ እንጅ ፅኑ እሰራት እንዲቀጣ መወሰኑ አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ዐ/ ሕግ በቀን 10/6/2003 ዓ/ም በ2 ገፅ መልስ ስጥቷል ፡፡ የመልሱ ፍሬ ሀሳብ የተባለው የቅጣት

ማቅለያ መክንያት ቅጣቱን ከመነሻው ዝቅ የሚደርግ ባለመሆኑ የጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ በመሆኑ እንዲፀና በማለት ተከራክሯል፡፡

የአመልካች ጠበቃ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡ በግራ ቀኙ የቀረበው ክርክር በአጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን በአቤቱታውም የቀረበውን ክርክር ከተያዘው ጭብጥና አግብበነት ካላቸው ሕጉ ጋር በማገናዘብ መርመሮታል ፡፡ እንደመረመረውም በዚህ ጉዳይ የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ከመነሻ ቅጣት / አምስት ዓመት ፅኑ እስራት / በታች የሚቀጣበት ምክንያት የለም የማለቱን አግባብነት በመመልከት መፍትሔ ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል ፡፡ በዚሁ መሰረት በሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ያስቀርባል ሲባል አመልካች ግጭቱን ካደረሰ በኂላ ማለትም የሐኪም ዕርዳታ እንድታገኝ ማደረጉ በወ/መ/ሕግ አንቀጽ 82/1/ /ሠ/ መሰረት ቅጣቱን ሊያቀለው የሚገባ ነው ወይስ አይደለም ? የሚል በመሆኑ ችሎቱም ከዚህ ጭብጥ አኳያ ብቻ በመመልከት መፍትሔ ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝቶታል፡፡ በመሠረቱ አንድ ጉዳት የደረሰበት ስው ወይም በአደጋ ላይ የሚገኘውን ሰው አለመርዳት የወንጀል ኃላፊነት የሚያስከትል መሆኑ በወ/መ/ሕግ ቁ 575 ሥር የተደነገገ ከመሆኑም በላይ ጉዳቱን ያደረሰው ተከሳሽ ራሱ በሆነበት ጊዜ ደግሞ የበለጠ የወንጀል ኃላፊነት የሚጥል ስለመሆኑ ከወ/መ/ ሕግ ቁጥር. 575 /2/ ሥር መረዳት ይቻላል ፡፡ ይሄንን ኃላፊነት ያልተወጣ ተከሳሽ ለዚህም ተጨማሪ የወንጀል ኃላፊነት በተደራራቢነት ሊጠየቅ እንደሚችልና አመልካች ወደ ሕክምና ማዕከል ማድረሱ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ የተጣለበትን ኃላፊነት መወጣቱን የሚያመለከት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 82/1/ /ሠ/ መሰረት ተከሳሽ በእዉነት የተፀፀተ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ሲገነዘብ ቅጣት ሊያቀልለት እንደሚችልና በእውነት ስለመፀፀቱ ከመገልጫዎቹ አንዱ በደል ለደረሰበት ሰው አስፈላጊውን እርዳታ ማድረጉ ሊሆን እንደሚችል ተቀምጧል ፡፡ ይሄ ማለት ግን ተከሳሽ ተበዳይን ወደ ሕክምና ማዕክል ማድረሱ ብቻ በፈፀመው ድርጊቱ በእውነት ተፀፅቷል የሚያሰኝ ሳይሆን ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ወይም በይግባኝ ያየው ፍርድ ቤት አጠቃላይ የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማትና በማመዛዘን የሚደርስበት መደመደሚያ ነው፡፡

አመልካች ተበዳይን ወደ ሕክምና ማዕክል ማድረሱ አጠቃላይ የክሱን ሂደት ከግምት በማስገባት አመልካች በእውነት ተፀፅቷል የሚያሰኝ ነው ወይስ አይደለም ? የሚለው ነጥብ የማስረጃ ምዘና በመሆኑና የዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን ደግሞ በሕግ መንግስቱ አንቀፅ 10 መሰረት መሰረታዊ የህግ ስህተት ማረም እንደመሆኑ መጠን የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የደረሰበትን መደምደሚያ መቀበሉ ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት አመልካች ተበዳይን ለሕክምና ማዕከሉ ማድረሱ ሌላ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በአመልካች ላይ የተጣለውን ኃላፊነት መወጣቱን እንጂ ቅጣቱን ለማቅለል የሚያበቃ አይደለም ማለቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘንም፡፡ በዚሁ መሰረት ቀጥሎ የተመለከተው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ 54154 በቀን 24.2.2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 195/2/ /መ/ መሰረት ፀንቷል፡፡ መዝገቡ ተዝግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመልስ ፡፡

ስ/ረ                                                            የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡